# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 74 ጥቅምት 5 2002 ዓ.ም ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**ማስታወቂያ**

የግንቦት 7 ድምጽ ከጥቅምት 15 ቀን 2002 ጀምሮ የአየር ሞገድ ለውጥ በማድረግ በተመሳሳይ ሰዓትና ቀናት በ7530 kHz በ41 meter band እና በ9610 kHz በ31 meter ባንዶች ላይ የሚተላለፍ መሆኑን እናስታውቃለን። **የግንቦት ድምጽ**

## ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ የመነጋገሪያ መድረክ ተገኝትው ለህዝብ ጥያቄ ምላሽ ሰጡ

የግንቦት 7 ሊ/መንበር የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ባለፈው ዕሁድ ጥቅምት 1 ቀን 2002 ኢካድፍ /ECADF/ በሚል ምህጻረ ቃል በሚታወቀው ታዋቂው የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች የመወያያ መድረክ/ ፓልቶክ ሩም/ ተገኝተው፣ የግንቦት 7ትን እንቅስቃሴን አስመልክቶ በመላው አለም የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እድምተኞች ላቀረቡት በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውን የግንቦት 7 ህዝብ ግንኙነት ክፍል ገልጾአል። ዶ/ር ብርሃኑ የሰጡትን መግለጫና ለተነሱት ጥያቄዎች የሰጡትን መልሶች በአንድ ጊዜ 500 ኮምፒውተሮችን ከሚያስተናግደው መደበኛ ክፍል በተጨማሪ እያንዳንዳቸው እስከ 250 በሚይዙ ሶስት የተለያዩ ክፍሎች መተላለፉን ያረጋገጠው የህዝብ ግንኙነት ክፍላችን በቦታ ጠበት ምክንያት መግባት የተሳናቸው በርካታ የግንቦት 7 ደጋፊዎችና አድናቂዎች በጓደኞቻቸውና የቅርብ ወዳጆችቸው አማካይነት በስካይፐ እና በስልክ ስከታተሉ አንደነበር ካሰባሰበው የህዝብ አስተያየት ለማወቅ መቻሉን አረጋግጦአል ።

2 ሰዓት ከ ሩብ ከፈጀ ከዚህ የጥያቄና መልስ ሥነሥረዓት ቦኋላ አዘጋጆቹ ለታዳሚው ባቀረቡት የገንዘብ መዋጮ ጥሪ መሰረት በርካታ ሰዎች ለግንቦት 7 ትግል ማካሄጃ የሚሆን ገንዘብ በኤልክትሮኒክስ የገንዘብ ማስተላለፊያ ዜዴ በመጠቀም የለገሱ መሆኑ ታውቆአል። ከዚህም በተጨማሪ በአገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ትግል በተለያየ መንገድ ሲደግፉና ሲረዱ የነበሩ በርካታ ሰዎች ግንቦት 7 የሚያካሂደውን ሁለገብ ትግል ለመቀላቀል በመወሰናቸው በድህረገጻችን አማካይነት የአባልነት ጥያቄ ማመልከቻ እንዳስገቡ ከድርጅት ጉዳይ ክፍላችን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ወቅቱ የሥራ እንጂ የወሬ አይደለም የሉት የንቅናቄያችን የግንቦት 7 ሊቀመንበር ፤ ኢትዮጵያ አገራችንን ከዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የጥፋት ተልኮ ለመታደግ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት ከፈጠረው ድህነትና ኋላቀርነት ተላቀን የተዋረደውን ብሄራዊ ማንነታችን ለማስመለስ ሁላችንም የምንችለውን ለማድረግ ዛሬውኑ አንነሳ በማለት ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን ሁላችንም ተግተን ከታገልን የጠላታችንን እድሜ ለማሳጠር ምንም ጊዜ እንደማይፈጅብን በእርግጠኝነት አረጋግጠዋል ።

## ባለፈው አመት ታህሳስ አሳፋሪ ሽንፈትና ውርደት ተከናንቦ ከሶማሊያ የተባረረው የወያኔ ጦር ባለፈው ቅዳሜና እህድ ድንበር አቋርጦ ሶማሊያን መግባቱን ሬዲዮ ፍራንስ ኢንተርናሽናል ዘገበ

ሬዲዮው ወያኔ በአንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የሶማሊያን ድንበርን አቋርጦ በመግባት ንጹሀን ሲቪሎችን ማሸበሩ በርካታ የሱማሌ ዘጎችንና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተማጓቾችን አጅግ አንዳስቆጣም ሳይደብቅ አጋልጦአል። በበርካታ መቶዎች የሚቆጠር የወያኔ ጦር የረባ ጥንካሬ እንደሌለው በሚነገርለት የሶማሊያ መንግስት ወታደር ጋር አብሮ ድንበሩን እንዳቋረጠ የገለጸው ዘገባ ወያኔ በርካታ በገጠር የሚኖሩ የሶማሊያን ዜጎችን ማገቱን ገልጿል።

ከሞቃዲሾ 300 መቶ ኪሌሜትር ርቃ በምትገኘው ቤልዴዎን በተባለች ቦታ ምእራባዊ ክፍል ያሉ ሶስት መንደሮች ውስጥ ገብቶ ብርበራ ያደረገው ወያኔ ምንም አይነት መሳሪያ እንዳላገኘ ታውቋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ሳሞራ የቀድሞ ወታደሮች እንዲባረሩ ትእዛዝ አስተላለፈ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ እየታየተ የመጣው የእርስ በርስ ሽኩቻ ያስደነገጠው አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ፣ በደርግ ዘመን ሲያገለግሉ የነበሩ መኮንኖችና ወታደሮች በረቀቀ ዘዴ እንዲባረሩ በኢታማጆር ሹሙ ሳሞራ የኑስ አማካኝነት ትእዛዝ ማስተላለፉ ታውቋል። ሳሞራ የኑስ የመከላከያና የፖሊስ የደህንነት ሃላፊዎችን በመሰብሰብ፣ በደርግ ዘመን ያገለገሉ ወታደሮች ፈጽመው ሊጠረጥሩ በማይችሉበት መንገድ እንዲወገዱና እርምጃውም በፍጥነት እንዲጀመር ሲል ትእዛዝ አስተላልፎዋል።

ወያኔ ወታደራዊ መኮንኖቹ እንዲወገዱ የሰጠው ምክንያት ግልጽ ባይሆንም ፣ ከወታደራዊ ምንጮች ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ወያኔ በሰራዊቱ ውስጥ በየጊዜው እየተፈጠረ ያለው የእርስ በርስ ሽኩቻ መንሰኤ በደርግ ዘመን ሲያገለግሉ የነበሩ የሰራዊቱ አባላት የፈጠሩት ነው ብሎ እንደሚያምን ለማወቅ ተችሎአል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ቴዲ የተከለከለውን ዘፈን ታዳሚው ዘፈነለት "ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ"፤ "ብርቱካን ትፈታ" መፈክሮችም ሲስተጋቡ ውለዋል

የጎዳና ተዳዳሪዎችን ለመርዳት ቴዲ አፍሮ ባለፈው ዕሁድ ጥቅምት 1 ቀን 2002 በአዲስ አበባ ስታዲዬም ባዘጋጀው የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ የተገኘው በብዙ ሺ የሚቆጠር የአዲስ አበባ ነዋሪ አርቲስቱ እንዳይዘፍን የታገደውን ልዩ ልዩ አገራዊ ዘፈኖችን ሲያቀነቅን እንደዋለ፣ በየመሃሉም "ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ፣ ብርቱካን ትፈታ!" በማለት መፈክሮችን ሲያሰማ እንደነበረ በስፍራው የነበረ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል። ገና ዝግጅቱ ሳይጀመር ከጠዋት ጀምሮ ወረፋ ለመያዝ በስተዲየሙ ዙሪያ ተሽኮልኩሎ ሲጠባበቅ የቆየው የከተማው ነዋሪ የስተዲየሙ በሮች ተከፍተው ወደውስጥ መግባት ከተጀመረበት ሰዓት ጀምሮ በእጁ የያዘውን የኢትዮጵያን ባንድራ በማውለብለብ ዝነኛውን የቴድ "ያስተሰሪያል"ን ዘፈን ከስተዲየሙ ጫፍ እስከ ወዲያኛው ጫፍ በመቀባበል ሲዘፍን ቆይቶአል። ቴዲ ወደመድረኩ ብቅ ካለ ቦኋላም ዘፈኑን ወደመፈክርነት በመለወጥ "ወያኔ ሌባ፣ ይለያል ዘንድሮ የእነመለስ ኑሮ፣ ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ፣ ይለያል ይለያል ፣ የወያኔ ጉዱ በቅርቡ ይታያል፤ ብርቱካን ትፈታ፣ ብርቱካን ጀግናችን፣ ቴዲ የኛችን" የሚሉት መፈክሮች በተደጋጋሚ መሰማታቸውን ዘጋቢያችን ገልጾአል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## አምባሳደር ተብየው ሳሙኤል አሰፋ ወደ አዲስ አባባ በድጋሚ ተጠራ፣ እንድርያስ እሸቴ ሊተካው ይችላል ተባለ

ህዝቡን በቅንነትና በታማኝነት ለማገልገል ቃል ገብቶ የተቀበለውን ዲግሪ ወደ ቆሻሻ ቅርጫት በመወርወር የነፍሰ ገዳዮች አገልጋይ መሆንን የመረጠው፣ በአሜሪካ የወያኔ አምባሳደር፣ ዶ/ር ሳሙኤል አሰፋ፣ ወደ አዲስ አባባ በድጋሚ መጠራቱ ሲታወቅ፤ ሌላው ተላላኪ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት የሆነው ፐ/ር እንድርያስ እሸቴ ደግሞ የሳሙኤልን ቦታ ሊይዝ እንደሚችል ያገኘነው መረጃ አመልክቷል። እንድርያስ እሸቴ ከአልኮል መጠጥና ከሲጋራ ብዛት ጋር በተያያዘ በተፈጠረበት የጤና መቃወስ ምክንያት ስራውን ማካሄድ በማይችልበት ደረጃ ላይ መገኘቱን የተናገሩት ምንጮች፣ ጤናውን በአሜሪካ ሆኖ እንዲከታተል በማሰብና በዚያውም ብዙ ጉለበት የማይጠይቀውን የወያኔን የዲፕሎማሲ ስራ እንዲሰራ በአምባሳደርነት ለመሾም መታቀዱን ምንጮች ተናግረዋል። ሳሙኤል አሰፋ በየጊዜው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስዩም መስፍን ጋር በሚፈጥረው አታካራ ምክንያት ስራውን ለመተው ማሰቡን የተናገሩት ምንጮች፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀጥሬ አልሰራም የሚል አቋም በመያዙ ወደ አስተማሪነቱ ሊመለስ ወይም በዩኒቨርስቲው ውስጥ እንድርያስ የጀመረውን የጥፋት ስራ ከግብ ለማድረስ በፕሬዚዳንትነት ሊሾም እንደሚችል መረጃው አመልክቷል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ከ40 በላይ የፍትህ ሚኒስቴር ሰራተኞች ለአገዛዙ ታማኞች አይደላቸሁም ተብለው ከስራቸው ተባረሩ

ሰራተኞቹ የተባረሩት "የገዢውን ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም አይደግፉም፣ የተቃዋሚዎች ደጋፊ ናቸው፣ በስራ ቦታ ላይ በመለገም የተቃዋሚ ድርጅቶችን ጥሪ ተግባራዊ ያደርጋሉ፣ የግንቦት 7 ወይም የአነግ ደጋፊዎች ናቸው" ወዘተ በሚል ምክንያቶች እንደሆነና ባልጠበቁበት ሰዓት ከሥራቸው እንዲባረሩ ለተደረጉት ለነዚህ ሰራተኞች የተነገራቸው ምክንያት ግን በቢፒአር ግምገማ መስፈርት ያለማሟላታቸው አንደሆነ ተደርጎ መሆኑን ለፍትህ ሚንስተር ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለግንቦት 7 ከሰጡት መረጃ ለማወቅ ተችሎአል። ቢፒአር ወያኔ ደጋፊዎቹ ያልሆኑትን በማባረር በምትካቸው ታማኝ የሚላቸውን ሎሌዎች መቅጠሪያ ዜዴ አድርግ እየተጠቀመበት መሆኑ ከምንጊዜዉም በላይ ለሁሉም ግልጽ እየሆነ መጥቶአል ። ወያኔ ከፍትህ ሚኒስቴር ያባረራቸውን ሰራተኞች በአዲስ ታማኝ ካድሬዎች ለመተካት መስከረም 8 ፣ 2002 ዓም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የስራ ማስታወቂያ ያወጣ ሲሆን፣ ካድሬዎቹ ምንም የስራ ልምድ አለመጠየቃቸውንም ለማወቅ ተችሎአል።

በተያያዘ ዜናም ከ30 በላይ የወያኔ ባለስልጣናት በህገወጥ መንገድ በአዲስ አባባ ከተማ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን መያዛቸውን በኢትዮጵያ ሬዲዮና በቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያቤቶች በተደረገው ግምገማ ወቅት ሰራተኞች ያጋለጡ ቢሆንም፣እስከ ዛሬ በባለስልጣናቱ ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን ምንጮቻችን ገለጸዋል።

ባለስልጣናቱ በህገወጥ መንገድ ቦታዎችን እየወሰዱ ቤቶችን በመስራት እንደሚያከራዩ ሰራተኞቹ መናገራቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ የወያኔ ባለስልጣናት ግን እንደዚህ የሚያደርጉትን ሰዎች ከመሾምና ከመሸለም በስተቀር ምንም እንደማያደርጓቸው ምንጮቻችን ተናግረዋል።

# በወያኔና አጫፋሪዎቹ አንገት ውስጥ ያጠለቅነውን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ሸምቀቆ በየእለቱ ይበልጥ እያጠበቅን የድላችንን ቀን እናቀርባለን!!!

የግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊቀመንበር የአዲስ ዓመት መልዕክት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ነፃነቱን ናፋቂ ሕዝባችን ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ማብራሪያ ሰጥቷል። በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊያትን በተመለከተ ደግሞ በቁጥር 71 ርዕሰ አንቀፅ ማብራሪያ ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ በተለይ ወያኔንና ተባባሪዎቹን የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግን (በሌላ አገላለጽ የግዢና ሽያጭ እቀባ ማድረግን) በሚመለከት የሚቀርቡልን ጥያቄዎች በመበራከታቸው ይህ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አስፈልጓል።

በመሠረቱ የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግ ቀላል ከሚባሉት የሰላማዊ ትግል ዓይቶች አንዱ ነው። ማናቸውንም ተቃውሞ በተከለከለባት አገራችን ግን ይህ የትግል ስልት የሁለገብ ትግላችን አካል መሆኑ ግድ ነው። ወያኔና ተባባሪዎቹን የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግ በትክክል በተግባር ላይ ከዋለ ኢትዮጵያዊያንን ለከፋ ጥቃት ሳያጋልጥ ጠላትን ማዳከም የሚችል ሁነኛ መሣሪያ ነው።

ወያኔንና ጀሌዎቹን የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግ በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. የወያኔና የደጋፊዎቹን የኢኮኖሚ አቅም ያሽመደምዳል፤
2. "ደንበኛ ንጉሥ/ንግሥት ነው/ናት" የሚለው የተለመደ የገበያ ኢኮኖሚ መርህ ተገልብጦ ሻጥ ጌታ፤ ገዢ ባርያ የሆነበትን የወያኔን የሽፍቶች ካፒታሊዝምን ያዳክማል፤
3. በሰብ አስባቡ በወያኔ እየተኮረኮሙ ያሉትን ኢትዮጵያዊያን ጥሮ አዳሪና ታታሪ ነጋዴዎችን ይደግፋል፤
4. ሁሉንም ሰው የትግሉ ተሳታፊ ያደርገዋል፤ በሕፃናት ሳይቀር ሊተገበር ይችላል፤
5. የሕዝባችንን የነፃነት ፍቅር እና በራስ የመተማመን ስሜትን ያጎለብታል፤
6. ድሃ ብንሆንም እንኳን ከወያኔ ለሚወረወር ፍርፋሪ ስንል ባርነትን የማንቀበል መሆኑን በተግባር ያረጋግጣል፤ እና
7. ሸቀጥ ወይም አገልግሎት ያልገዛን ለቅሞ ለማሰር የሚያስቸግር በመሆኑ ደጋፊዎቻችንን ለከፋ ጥቃት አያጋልጥም።

የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግ በኢትዮጵያችን ውጤታማ የትግል ስልት ስለመሆኑ ብዙዎች ይጠራጠራሉ። ይህ ጥርጣሬ በተወሰነ መጠን ምክንያታዊ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ የእለት ተእለት ግዢን በትግል መሣሪያነት መጠቀም አልተለመደም። ይሁን እንጂ ይህ ባጭር ጊዜ ሊቀየር የሚችል እንደሆነ ፍንጮች ታይተዋል። በምርጫ 97 ማግስት ሕዝብ በራሱ ተነሳሽነት የአላሙዲን ንብረት በሆነው በሞሃ ለስላሳ መጠጦች በተለይም በፔፕሲ ኮላ ላይ የጣለው ማዕቀብ ውጤታማ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ይህ ማዕቀብ ሞሃን ለከፍተኛ ኪሳራ የዳረገው ሲሆን ሕዝብ በአላሙዲን ተግባራት ምን ያህል መማሩን በሚገባ ገልፆበታል። በእንዲህ ዓይነቱ የግዢ እቀባ በአንዳንድ ዘርፎች አፋጣኝ ውጤት ማምጣት ይቻላል። ለምሳሌ የወያኔ ሆቴሎችንና ምግብ ቤቶችን ባጭር ጊዜ ውስጥ በገበያ እጦት ከስረው እንዲዘጉ ማድረግ ይቻላል። በውጭ አገራት የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወደ አገር ቤት የሚልከው ገንዘብ ለወያኔ የውጭ ምንዛሪ ረሃብ ማስታገሻ በማይሆን መንገድ ቢያደርገው ወያኔን በእጅጉ የሚያዳክም ተግባር ነው። በአንዳንድ ዘርፎች ደግሞ እቀባው ከሚያደርሰው ኪሳራ በላይ መልእክቱ ዋጋ አለው። ለምሳሌ እያንዳንዱ ነፃነቱንና አገሩን የሚወድ ዜጋ በውጋጋን ባንክ ያለውን አንዲትም ብር ቢሆን ወደ ሌሎች ባንኮች ቢያዛውር በዚህ ተግባር ውጋጋን ባይከስር እንኳን የመልእክቱ ክብደት ምን ያህል ከፍተኛ እንደሚሆን ልብ ማለት ያሻል።

ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያዊ ሸማች የሚያወጣት እያንዳንዷ ብር ሸቀጥ ወይም አገልግሎት ከመግዛት በተጨማሪ መልእክት አስተላላፊ እንድትሆን ማድረግ መቻል አለብን። ከአሁን በኋላ ከወያኔ ወይም ከባንዳ አንዳችም ነገር ላለመግዛትም ሆነ ላለመሸጥ ወስነን ተግባራዊ ማድረግ መቻል አለብን። ይህ መከወን የሸማች በራስ የመተማመን ስሜትን ያዳበራል፤ የወያኔን ቅስም ይሰበራል፤ ልንገነባ የምንፈልገውን የነፃ ማኅበረሰብን የሥነልቦና መሠረት ይጥልልናል። ለዚህ ሩቅ ዓላሚ ትግል አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ጥሪዓችንን ደግመን ደጋግመን እናቀርባለን።

"ከወያኔ ድርጅቶች ሌላ አማራጭ ሻጮች ባይኖሩስ ምን እናደርጋለን?" የሚል ስጋት በብዙዎች ዘንድ መኖሩ ከሚደርሱን ጥያቄዎች መገንዘብ ይቻላል። እኛ እስከምናውቀው አማራጭ ፈጽሞ የሌለባቸው ዘርፎች የሉም። ይልቁንስ "በምርጫ አጣን ሰበብ" ከወያኔ ድርጅቶች ጋር እየነገድን ገበያውን መቶ በመቶ እንዲቆጣጠሩት ሁኔታዎችን አናመቻችላቸው። በሌላ በኩል ደግሞ አማራጮች በጠበቡበት ሁኔታ ተጨማሪ አማራጮችን መፍጠር የትግሉ አንዱ አካል ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። ለምሳሌ ወያኔ የማይቆጣጠራቸው የገንዘብ መላኪያ መንገዶችን ማፈላለግ፤ ከሌሉም መፍጠር በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሥራ መሆን ይኖርበታል። በወያኔ አንገት ውስጥ ያጠለቅነውን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ሸምቀቆ የማጥበቅ ሥራ ከግለሰብ አልፎ በየአገራቱ የሚገኙ የግንቦት 7 ህዋሳት የእለት ተእለት ሥራ መሆን ይኖርበታል::

ሌላው የተለመደው ጥያቄ "እነማን ናቸው ድርጅቶቹ?" የሚለው ነው። የድርጅቶቹ ሙሉ ዝርዝር ማውጣት አስቸጋሪ ነው። የድርጅቶች ዓይነትም እንደየቦታውና ሁኔታው ይለያያል። እያንዳንዱ ህዋስ እና እያንዳንዱ ግለሰብ በአካባቢው ባሉት የወያኔና አጫፋሪዎቻቸው ንግዶችን ላይ ማዕቀብ መጣል ይኖርበታል። የወያኔና አሽከሮቻቸውን ድርጅቶች በምንለይበት ወቅት መመዘኛችን ከወያኔ መብት ረገጣ እንጂ ከሌላ ምንም ነገር ጋር እንዳይያያዝ መጠንቀቅ እጅግ አስፈላጊ ነው:: በተጨማሪም ትኩረታችን ትላልቆቹ ኩባንያዎች ላይ ቢሆንም በየሰፈሩ የሚገኙ የወያኔና አሽከሮቻቸው ትናንሽ ንግዶችም ጭምር መካተታቸውን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ለመነሻ ያህል ዋና ዋና የወያኔ የንግድ ተቋማትን ስም ዝርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል።

**የኤፈርት ድርጅቶች**

መሶበ የኮንስትራክሽን ግብዓት ማምረቻ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ፣ አዲስ የመድሃኒት ማምረቻ፣ ኢዛና የማዕድን ልማት፣ ጉና የንግድ ድርጅት፣ ሕይወት የግብርና ሜካናይዜሽን፣ ሳባ እብነ በረድ ማምረቻ፣ ሼባ የቆርቆሮ ፋብሪካ፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ አልሜዳ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ኤክስፕረስ የትራንዚት አገልግሎት፣ ኢትዮጵያን እንወቅ አስጎብኚ ድርጅት እና ትራንስ ኢትዮጵያ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት

**ደጀና ኢንዳውመንት**

ብሩህ ተስፋ ፕላስቲክ ፋብሪካ፣ ማይጨው ፓርቲክል ቦርድ ፋብሪካ፣ ዲማ የማር ማጣሪያ፣ አላጌ ደንና የደን ውጤቶች፣ ናሽናል ጂኦ-ቴክስታይል እና አበርደሌ የእንስሳት ማድለቢያና ኢክስፖርት ድርጅት

**በአክስዮን ሽፋን የተቋቋሙ**

ሰላም ትራንስፖርት፣ ሰገል ኮንስትራክሽን፣ ሜጋ ኔት ኮርፖሬሽን፣ ሃይቴክ ፓርክ፣ ፋና ዲሞክራሲ፣ ኤክስፕረስ ትራንዚት፣ ኢትዮ ሬንታል፣ አዲስ ኮንሰልታንሲ፣ መስከረም ኢንቨስትመንት፣ አፍሪካ ኢንሹራንስ፣ ግሎባል አውቶ ስፔርፓርት፣ አዲስ ኢንጅነሪንግ፣ ተስፋ የእንስሳት ማድለቢያ፣ አምባሰል ኮሜርስ፣ ዲንሾ አክ ማኅ፣ ብሩክ ኬሚካል፣ ዳሸን ቢራ ፋብሪካ፣ ኤክስፕረስ ኢትዮትራቭል አገልግሎት፣ ብርሃን የሕንፃ ኮንስትራክሽን፣ ኮከብ የመድሃኒት አስመጪዎች፣ ናሽናል ኤሌክትሮሜካንካል፣ ቢፍቱ ዲንሾ፣ ወንዶ ትሬዲንግ፣ ሻላ አድቨርታይዝመንት፣ ትራንስ ኢትዮጵያ፣ ውጋጋን ባንክ፣ ዋልታ፣ ማርታ የዶሮ እርባታ፣ ጥቁር አባይ ትራንስፖርት

**የሚድሮክ ኢትዮጵያ (የአላሙዲን) ድርጅቶች**

ሚድሮክ የወርቅ ማዕድን፣ ኤልፎራ አግሮ_ኢንዱስትሪ፣ ሁዳ ሪል እስቴት፣ ኮምቦልቻ ብረታ ብረት ምርቶች ኢንዱስትሪ፣ ዘመናዊ የሕንፃ ኢንዱስትሪ፣ ትረስት የጥበቃና የሰው ኃይል አገልግሎት፣ አዲስ ሆም ዲፓ፣ ትራንስ ኔሽን ኤርዌይስ፣ አዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ፣ ዋንዛ ፈርኒሺንግስ ኢንዱስትሪ፣ ዴይላይት አፕላይድ ቲክኖሎጂስ፣ ሰሚት ኢንጂነሪንግ ፕላስቲክስ፣ ብሉ ናይል የፒፒና ክራፍት ወረቀት ከረጢት ማምረቻ፣ ሬይንቦ የመኪና ኪራይና የአስጎብኚ አገልግሎት፣ ዩናይትድ የአውቶሞቢል ጥገና አገልግሎት፣ ዩኒቲ ዩኒቨርስቲ፣ መቻሬ ከፍተኛ ክሊኒክ

በወያኔና አጫፋሪዎቹ አንገት ውስጥ ያጠለቅነውን የኢኮኖሚ ማዕቀብ ሸምቀቆ በየእለቱ ይበልጥ እያጠበቅን የድላችንን ቀን እናቀርባለን!!!

ማስታወቂያ
የግንቦት 7 ድምጽ የአድማጮቹን አስተያየት በስልክ ጭምር ለመቀበል እንዲያስችለው አንድ የስልክ መስመር ከፍቶአል ። ስለዚህ ስለፕሮግራማችን አስተያየት ሲኖራችሁ በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661 ልትደውሉልን የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ኢትዮጵያን ከዘረኞች ማደን የዛሬዉ ትዉልድ ታሪካዊ ኃላፊነት ነዉ!

ኤፍሬም ማደቦ

የኢትዮጵያ ህዝብ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር በኖረበት በሺዎች በሚቆጠር ዘመኑ ዉስጥ ብሔራዊ ነፃነቱን ተቀምቶ የኖረበት አንድም ግዜ የለም። የፋሽስት ጣሊያን ወራሪዎች አዲስ አበባን በተቆጣጠሩበት ከ1928–1933 ድረስ ባሉት 5 ዐመታት ዉስጥም ቢሆን የኢትዮጵያ አርበኞች ግራዚያኒና ተከታዮቹ "ምነዉ በቀረብን" እስኪሉ ድረስ እረፍት ነሷቸዉ እንጂ ለጣሊያን የተንበረከኩበት አንድም ቀን እንዳልነበረ የጣሊያኖች የራሳቸዉ ታሪክ ይመሰክራል። ዛሬ ከአባቶቹ በተለየና ሻል ባለ ሁኔታ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ለእናት አገሩ ለኢትዮጵያ ያለዉ ፍቅር ከአባቶቹ የተለየ ባይሆንም ያ' በአባቶቻችን ዉስጥ የነበረዉ "ከኔ በፊት" ለአገሬ የሚለዉ በተግባር የተጠቀለለ መፈክር ከዛሬዉ ትዉልድ እምብዛም አይሰማም። በተለይ ምሁሩ፤ ነጋዴዉና፤ ከፍተኛና መካከለኛ ገቢ እያገኘ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ለህዝብ መብትና ነፃነት ከመታገል ይልቅ ተራ እየጠበቀ ከሚመጣዉ አምባገነን ጋር ተመሳስሎ መኖርን የመረጠ ይመስላል። ስለሆነም ዛሬ ይህ ነዉ የሚባል የተደራጀ ተቃዉሞ እንደሌለባቸዉ የተረዱት የወያኔ ዘረኞች የኢትዮጵያን ህዝብ እንዳሰኛቸዉ ያስሩታል፤ ከአገሩ እንዲሰደድ ያስገድዱታል ሸንጡን ገትሮ የሚታገላቸዉን ደግሞ አሰቃይተዉ ይገድሉታል።

የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነፃነት በተመለከተም ቢሆን በመለስ ዜናዊ ዘመን የኢትዮጵያ ነፃነት ከዉጭ በመጣ ወራሪ ኃይል ባይደፈርም የግዛት አንድነቷና ክልሏ ግን እንደ ቡሄ ዳቦ እየተቀረሰ ሆ" ብሎ ለመጣ ሁሉ እየተሰጠ ነዉ።ከትናንት ወዲያ ያካሄድነዉ ትግል ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ነበር፡ የትናንቱ ትግላችን ደግሞ ከዘረኝነት ጋር ነበር፡ የዛሬዉ ትግላችን ግን ከወያኔ አይን ያወጣ የአገር መሸጥ ክህደት ጋር ሆኗል። እንግዲህ እንደዚህ አይነት እጥፍ ደርብ ትግል ፊት ለፊቱ ላይ የተደቀነበት ህዝብ ጠላቱን ፊት ለፊት እያየ ዝም የሚልበት ግዜ ቀርቶ ከወዳጁም ጋር ቢሆን የሚዝናናበት ግዜ ሊኖረዉ አይገባም።

ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ የዉስጣችንን ዝምታ እየለካና ለአፍታ ብቻ ገንፍሎ የሚቀዘቅዘዉን ቁጣችንን እየተመለከተ ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ዘመቻዉን በስፋት ተያይዞታል። ዛሬማ አይናችን እያየ የጀግኖች አባቶቻችንን አፅም የተሸከመዉን በደም የታጠረ መሬት ለጎረቤት አገር ለማስረከብ በዝግጅት ላይ ይገኛል። ከአንድ አመት በፊት ከሀዲዉ መለስ ዜናዊ ለሱዳን የሚሰጠዉን መሬት አስመልክቶ ለዚያ እንቅልፋም ፓርላማዉ ንግግር ሲያደርግ እንደዚህ ነበር ያለዉ "የሁለቱ አገሮች ድንበር ሲከለል ከሁለቱም አገሮች በኩል የሚፈናቀል ሰዉ አይኖርም"! መለስ ዜናዊ ወይም የዘመናችን ሱልጣን ኢብራሂም ይህንን እጅግ አሳፋሪ የሆነ ንግግር ሲያደርግ ፓርላማዉ ዉስጥ ይሰማ የነበረዉ ጭብጨባና ጩኸት አዳራሹን መለስ ዜናዊ ሳይሆን ኦመር አልበሽር የሚናገርበት የሱዳን ፓርላማ አስመስሎት ነበር።

በአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ዉጭ የምትኖረዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ መሪዎች እንደ ጥላ ብቅ ብለዉ የሚጠፉ ግዜያዊ ፍጡሮች ናቸዉ፤ ፓርላማም ቢሆን የሚወክለዉን ህዝብ እምነትና ፍላጎት አስካላንፀባረቀ ድረስ እየተተካ የሚያልፍ ግዜያዊ አካል ነዉ፡ አገርና ህዝብ ግን ተከታታይነትና ዘለአለማዊነት ያላቸዉ ቋሚ ክስተቶች ናቸዉ። ዛሬ በዉጭዉ ዓለም ተመችቶህ የምትኖረዉም ሆንክ አገር ዉስጥ በዘረኝነት ሠንሰለት ታስረህ የኑሮን መከራ የምትገፋዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልታስተዉለዉ የሚገባ አንድ ትልቅ ጉዳይ አለ፤ እንደ መለስ ዜናዊ አይነቱ ከዛሬ በኋላ 30 ዐመት እንኳን የመኖር ዋስትና የሌለዉ ከሀዲ ሰዉ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ አሰቃቂ በደል በአገራችን ላይ ሲፈፀም ዝም ብለህ ልትመለከት በፍፁም አይገባም።መለስ ዜናዊ ከሞትኩ ላይቀር ብሎ የሚፈፅመዉን ብሄራዊ በደል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሞት አንደሆነ አይቀርም ብሎ አጥብቆ መዋጋት አለበት።

የእናት አገራችን ኢትዮጵያ የግዛት አንድነት አደጋ ላይ በወደቀበት ግዜ ሁሉ ልጆቿ የአገር አድን ጥሪዋን እየተቀበሉ አገራቸዉን ከአደጋ አድነዋል። የሚገርመዉ በአባቶቻቸን ዘመን የነበረዉ ትዉልድ ብዙም ጥሪ የማያስፈልገዉ ወይም ዘምቶ ለአገሩ ካልተዋጋ እየተንሰቀሰቀ የሚያለቅስ አገር ወዳድ ትዉልድ ነበር። ዛሬም ቢሆን አገሩን የማይወድ ኢትዮጵያዊ ቢኖር ለሆዱ ብቻ ያደረ ባንዳ ነዉ እንጂ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ አገሩን ይወዳል።ሆኖም የዛሬዉ ትዉልድ አገር ወዳድነት አገራችን ከልጆቿ ከምትጠብቀዉ መስዋዕትነት አኳያ ሲታይ በእርግጥ አገራችንን እንወዳለን ወይ የሚል ጥያቄ ዉስጥ ከትቶናል።

ባለፉት 18 ዐመታት በተከታታይ እንዳየነዉ ወያኔዎች በንፁሀን ዜጎች ላይ የሚፈፅሙትን አረመኔያዊ ጭፍጨፋና በአገራችን የግዛት እንድነት ላይ የሚሸርቡትን ተደጋጋሚ ሴራ ከመቃወም አልፈን አገራችንን ከወያኔ አደጋ ለማዳን የወሰድነዉ ተግባራዊ እርምጃ የለም።እዚህ ላይ በጣም የሚያሳዝነዉ ተቃዉሞአችንና ቁጣችንም ቢሆን የሚገለፀዉ ዘላቂነት ባለዉ መልኩ ሳይሆን ወያኔ በደል በፈፀመበት ማግስት ብቻ ነዉ። እንደዚህ አይነቱ ኢትዮጵያዊነት ያልዳሰሰዉ ባህሪይ ደግሞ ከሀዲዉ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የጀመረዉን ዘመቻ ካለመሰናከል እንዲገፋበት አስችሎታል።

ዛሬ ኢትዮጵያችን ላይ ከተደቀኑት ከፍተኛ አደጋዎች አንዱና ዋናኛዉ መለስ ዜናዊ የአገራችንን መሬት ለሱዳን ለመስጠት ከግዜ ጋር የሚያደርገዉ እሽቅድምድም ነዉ፤ ኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ ዉስጥ የሚታየዉ ትልቁ ድራማ ደግሞ ህዝብ የመለስ ዜናዊንና የአልበሺርን የድንበር ስምምነት እንዳይቀበል ከመቀስቀስና ከማደራጀት ይልቅ የመለስ ዜናዊን ንግስና ለማድመቅ የሚደረገዉ እስጥ አገባ ነዉ። የሚወዳት አገሩ የግዛት እንድነት እንደ ዛሬዋ ኢትዮጵያ በራሷ መሪዎች የተናጋ አገር ዉስጥ የሚኖር አንድ ኃብታም ነጋዴ ከሰራተኞቹ አንዱን ጠርቶ የምትፈልገዉን ነገር ንገረኝና እሰጥሀላሁ ይለዋል - ሰራተኛዉም ጥቂት አሰበና ጌታዬ በወርቅ የተሰራ ሳጥን ይስጡኝ ይላቸዋል፤ ነጋዴዉም ፍላጎቱ ገርሟቸዉ ምን ልታስቀምጥበት ብለዉ መለሱለት ይባላል።ዛሬ አዲስ አበባ ዉስጥ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቆርጦ ከተነሳ ኃይል ጋር የሚደረገዉ ምንም አይነት ድርድር እላይ ከተጠቀሰዉ ነጋዴና አገልጋያቸዉ ጥያቄና መልስ ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

ዛሬ ገፍቶ በመጣዉ የወያኔ የመሬት ሽያጭ ዋዜማ የጎበዝ ያለህ እያለ የሚጮኸዉን የኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ የሚያሳስቡት ብዙ ነገሮች አሉ።መለስ ዜናዊ የህዝብን ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በእቅዱ መሠረት የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ቢያስረክብ እንኳን ዳር ድንበሩ በባዕድ ሲረገጥ ዝም ብሎ የሚመለከት ህዝብ የለምና የኢትዮጵያ ህዝብ መሬቱን ለማስመለስ መዋጋቱ አይቀርም - እዚህ ላይ ትልቁ ጥያቄ ዛሬ በወያኔ ስር የሚገኘዉ የመከላከያ ሠራዊት የወያኔን ትዕዛዝ ተቀብሎ እናቱንና አባቱን ይወጋል ወይስ አንዳባቶቹ አገሩን ከሚሸጡ ጠላቶቹ ጋር ይዋጋል? ይህ ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀ ሠራዊት አባቶቹ በጦርና በጎራዴ ያስከበሩትን መሬት መሪ ተብዬዉ ለጎረቤት አገር ሲሸጥ ሽያጩን ላለመቀበል ከአገሩ ህዝብ ጎን ይቆማል ወይስ የወያኔን የመሬት ሽያጭ ዉል ለማፅናት ከዘረኞችና ከባእዳን ጎን ይቆማል?

ይህ ዛሬ በወያኔ ስር ለሚገኘዉ የመከላከያ ሠራዊት የቀረበለት ታሪካዊ ጥያቄ በወጭም ሆነ በአገር ቤት ለሚገኘዉ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚቀርብ ጥያቄ ነዉ። ነግደህ ለማትረፍ የምትሯሯጠዉ ነጋዴ፤ በጥናትና ምርምር ዘርፍ የተሰማራኸዉ ምሁር፤ በዉጭ አገር ጎንበስ ቀና እያልክ የቋጠርካትን ገንዘብ ይዘህ አገር ቤት የምትሄደዉ ኢትዮጵያዊና የወደፊቷን ኢትዮጵያ ተረካቢ የሆንከዉ ወጣት በየተሰማራቸሁበት የስራ መስክ ከወያኔ ጋር ትንቅንቅ የምታደርጉበት ግዜ ዛሬ ነዉ። አለዚያ ነገ ዛሬ እያልን ለወያኔ ግዜ ከሰጠነዉ ምሁሩ የሚመራመርበት ቦታ፤ነጋዴዉ ሽጦ የሚያተርፍበት ዘርፍ ወጣቱ ደግሞ ነገ የሚረከበዉ አገር አይኖርም። አገራችን ዉስጥ ዘረኝነት ነግሶ መሬታችን ለጎረቤት አገር እየተሸጠ ሠላም የለምና "ሠላማዊ ትግል" የሚለዉን የወያኔ የማታለያና የግዜ መግዣ መፈክር ችላ ብለን የምንታሰረዉ ታስረን የምንሞተዉ ሞተን የአገራችንን ህዝብ ከረሀብና ከችግር አገራችንን ደግሞ ከመበታተን የማዳን ግዜ ዛሬ ነዉ። በነገራችን ላይ መብታችንንና ነፃነታችንን አስከብረን በሠላም ለመኖር የእኛ ምርጫ ምን ግዜም ቢሆን ሠላማዊ ትግል ነዉ። ነገር ግን ሠላማዊ ትግል ሠላም የገባዉና የሠላምን ቋንቋ የሚናገር አቻ ያስፈልገዋል። ስለዚህ ወያኔ ሠላምን በትክክል እስኪረዳና ለኛም ሆነ ለወያኔ ሠላማዊ ትግል የበላይና የበታች የሌለበት ሆኖ ህዝብን በምልዐት የሚያሳትፍ ትግል እስካልሆነ ድረስ የኛም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ ሁለገብ ትግል ይሆናል። እዚህ ላይ የወደፊቷን ኢትዮጵያን ተረካቢ የሆነዉ ወጣቱ ትዉልድ ልብ እንዲለዉ የምንፈልገዉ ነገር አለ።

በቅርቡ ተንኮለኛዉ መለስ ዜናዊ የልጁን የፖለቲካ ዝንባሌ አስመልክቶ ምን ትመክራታለህ ተብሎ ሲጠየቅ -እንዲህ ነበር ያለዉ "ፖለቲካ የሚቻል ነገር አይደለም በተቻለ መጠን እጇን ከፖለቲካ ብትሰበስብ ደስ ይለኛል" የኢትዮጵያ ወጣት ሆይ መለስ ዜናዊ ይህንን ምክር መሰል ማስጥንቀቂያ የሰጠዉ ለልጁ ሳይሆን ላንተ ነዉ፤ ልጁማ የሱን ወንበር ለመዉረስ ለንደን ገብታ ስልጠናዋን ጀምራለች። ወያኔዎች ባንተ ዉስጥ ያለዉን ቆራጥነትና እምቅ ኃይል ስለሚያዉቁ እንዳትነሳና እንዳትታገላቸዉ እነሱ ምን ግዜም ገዢዎች አንተ ግን ተገዢ ሆነህ እንድትኖር የፈጠሩት ዘዴ ነዉና አትስማቸዉ! ይልቁንም እነዚህን ዘረኞችና ከፋፋዮች ለማጥፋት የሚተማመኑብህንና የምታምናቸዉን መሪዎችህን ተከትለህ ለወሳኙ ፍልሚያ ክንድህ አንሳ!

ነፃነት እኛ ሰዎች ወደዚህ ዓለም ስንመጣ አብሮን የሚመጣና ከግለሰብ፤ ከህብረተሰብ፤ ከመንግስትና ከአካባቢ ጋር የምናደርጋቸዉን ግኑኝነቶች ሁሉ የተሟላ የሚያደርግ ተፈጥሮ ያደለን ስጦታ ነዉ። ነፃነት ማንም ሊቀማን ወይም መጥኖ ሊሰጠን የማይገባ የተፈጥሮ ፀጋ ነዉ። ይህንን የተፈጥሮ ፀጋ ተቀምቶ እየተገዛ በሠላም የኖረ አንድም ህዝብ የለም። ለሌሎች ሠላምና ነፃነት የተዋደቀዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ቀንና ማታ ልጆቹን እየገደሉ የሚያስለቅሱትን የቀን ጅቦች ቀርቶ ለኃዘን ያደገደገዉን ነጠላም የሚሸከምበት ትከሻዉ ሳስቷል።

ወያኔ ሠፈር ከበሮ ሲደለቅ ሁሉም ሰዉ የደላዉ ወይም የወያኔ መንጋ ጠግቦ ሲያገሳ ህዝብ በልቶ ያደረ የሚመስላቸዉ የወያኔ ዘረኞች የረሀብ ዘመን አበቃ የሰላም ዘመን ተጀመረ ብለዉ ካወጁ 18 አመት አለፋቸዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ወያኔ አዲስ አበባን ከረገጠበት ቀን ጀምሮ ሆዱ ምግብ ጠግቦ አዕምሮዉ ሠላም አግኝቶ ያደረበት አንድም ቀን የለም። ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ የነፃነትና የዲሞክራሲን አስፈላጊነት አሳንሶ ለማቅረብ የተለያዩ ስልቶቸችን ይጠቀማል። ከእነዚህ ስልቶች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ህዝብ በልቶ እስካደረ ድረስ ነፃነትና ዲሞክራሲ ቀስ ብለዉ ሊመጡ የሚችሉ ነገሮች እንደሆኑ ደጋግሞ መናገር ነዉ። ለዚህ ነዉ ዛሬ መለስ ዜናዊ ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚጮኸዉ ስለህዝብ መብትና ነፃነት መከበር ሳይሆን ስለዚያ የሱና የብጤዎቹ የባህር ማዶ የባንክ ሂሳብ በጨመረ ቁጥር አደገ ስለሚለዉ አኮኖሚ ብቻ የሆነዉ።

ለመብትና ለነፃነት የሚደረግ ትግል እኔን አይመለከተኝም ብለን ለሌላ የምናስተላልፈዉ ጉዳይ አይደለም።ነፃነት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የግል ኃብት ስለሆነ ለነፃነት የሚደረገዉ ትግልም የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል። አንዱ ታጋይ ሌላዉ ተመልካች፤ አንዱ ለአገሩ ሟች ሌላዉ ለሆዱ የሚኖርበት ዘመን ማብቃት አለበት።

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ያለዉ ብቸኛ አማራጭ በአጭር ታጥቆ የወያኔን ስርአት ለማስወገድ ትግሉን ማፋፋም ብቻ ነዉ። ይህ ለነፃነታችን የምናደርገዉ ትግል ደግሞ በመላዉ ዓለም የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ በመተጋገዝ የሚታገለዉ የጋራ ትግል ነዉ እንጂ አገር ዉጭና አገር ዉስጥ እየተባለ ሁለት ቦታ የሚከፈል ትግል አይደለም። አገር ቤት የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ የወያኔን ዘረኝነት፤እስርና ድብደባ ፊት ለፊት የሚጋፈጥ በመሆኑ የነፃነት ትግሉ ቀጥተኛ ባለቤት ነዉ። የአገር ቤቱ ኢትዮጵያዊ የመሰብሰብ፤የመደራጀትና ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነት ስለሌለዉ የዚህን ህዝብ ጩኸት መጮህና ለህዝባዊ ትግሉ ድርጅታዊ ቅርፅ የመስጠቱ ሃላፊነት በነፃዉ አለም የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ ሀላፊነት ነዉ።

ባለፉት 18 አመታት ከወያኔ ዘረኝነት፤ እስርና ድብደባ አምልጠዉ አዉሮፓና አሜሪካ ገብተዉ ኑሮ የጀመሩ የኢትዮጵያ ምሁራን ቁጥር የትዬለሌ ነዉ። ሆኖም የኢትዮጵያ ህዘብ የሚኖርበትን አስከፊ ሁኔታ በዉል የሚያዉቀዉ ይህ የምሁር ህብረተሰብ የኢትዮጵያን ህዝብ እሱ አምልጦ ከመጣበት ከዚያ ሰዉ በላ ስርዐት ነፃ ለማዉጣት የሚያደርገዉ ጥረት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነዉ። አገር ዉስጥ የሚኖረዉ ምሁርም ቢሆን ወይ የወያኔ ሎሌ ነዉ አለዚያም እሱም እንደ ጓደኞቹ ከአገር የሚወጠበትን ቀን ይጠብቃል እንጂ የህዝብን መብትና ነፃነት ለማስከበር ከወያኔ ጋር ፊት ለፊት የሚጋፈጠዉ ምሁር ቁጥር ዝቅተኛ ነዉ።

አዉሮፓዉያንና አሜሪካዉያን በተዋደቁለት ነፃነት ግድግዳ ስር ተከልለህ የወገኖችህን ሰቆቃ የረሳኸዉ ኢትዮጵያዊ ሆይ በዚህ የተዉሶ ነፃነት ከሚገኝ ኃብትና ደስታ ይልቅ ለአንድ ቀንም ቢሆን ተወልደህ ባደግህበት መሬት ላይ ስብዕናህ ተከብሮ ነፃነትህን እንደጨበጥክ ብትሞት ያ' የክብር ሞት ነዉ።እናትና አባቱ በዘረኞች እየተገዙ እሱ በባዕድ አገር እየኖረ ነፃነቴ ተከብሮልኛል ብሎ ከሚኩራራ ምሁር የበለጠ እሱነቱን ሽጦ በባርነት ዉስጥ የሚኖር ሰዉ የለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ እስከዛሬ ማለት የሚገባህን ሁሉ ብለሃል ከአሁን በኋላ የቀረህ ከወያኔ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠህ በኃይል የተቀማኸዉን ነፃነት በኃይል ማስመለስ ብቻ ነዉ። ህዝብ መሪዉን እንጂ አሳዳጁን፤የሚያበለፅገዉን እንጂ የሚዘርፈዉን፤ የአገሩን ዳር ድንበር የሚያስከብርለትን እንጂ ግዛቱን እየሸረሸረ ለባዕድ የሚያድልን ሰዉ መሪ ብሎ አይመርጥምና ይህንን ምርጫ የሚሉትን የዘረኞች ማዘናጊያ ችላ ብለህ ዛሬ ነገ ሳትል ክንድህን በወያኔ ላይ አንሳ! ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት ሁኔታ እኔ ልቅደም አንተ እየተባባልን ጠላታችንን ለመምታት የምንሽቀዳደምበት ግዜ ነዉ እንጂ ገሚሱ ሲታገል ሌላዉ ቆሞ የሚመለከትበት ግዜ አይደለም። ዘረኞች እኛን ለመግዛትና አገራችንን ለመከፋፋል እንቅልፍ አጥተዉ የሚያድሩ ከሆነ እኛማ ለነፃነታችንና ለአገራችን አንድነት ምን የማናደርገዉ ነገር ሊኖር ይችላል? ሞት እንደሆነ መከፈሉ የማይቀር የህይወት ዕዳ ነዉ፤ እንግዲህ የአገርን ዕዳ ሳይከፍሉ መሞት ለትንሳኤም ቢሆን አይበጅምና ይህ ትዉልድ- ቆሞ በህይወቱ ተሰዉቶ በሞቱ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ማረጋገጥ አለበት!

## ሳሞራ የቀድሞ ወታደሮች እንዲባረሩ ... ከገጽ 1 የዞረ

ይሁን እንጅ በሰራዊቱ ውስጥ ለተፈጠረው መቃቃር ዋነው መንስኤ የቀድሞ ወታደሮች መገኘት አለመሆኑን የሚናገሩት ምንጮች፣ ይልቁንም በሰራዊቱ ውስጥ አንደኛ ደራጃ ዜጋና ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ የሚል ክፍፍል መፈጠሩ ችግሩን እንዳባባሰው ተናግረዋል። አንደኛ ደረጃ ዜጋ የሚባሉት የትግራይ ተወላጅ መኮንኖች፣ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ የሚባሉት ደግሞ የተቀሩት ኢትዮጵያውያን መኮንኖች መሆናቸውን የተናገሩት ምንጮች፣ አንደኛ ደረጃ ዜጎች ሁለተኛ ደረጃ ዜጎችን እንደ ቤት አሽከራቸው እንደሚያዙዋቸው አስረድተዋል። በአንደኛ ደረጃ ለሚታዩት የህወአት አባላት የደሞዝ፣ የህክምና፣ የትምህርት፣ በሰላም አስከባሪነት ሥም ዳጎስ ያለ የውሎ አበል ጥቅም በሚያስገኝ ስራና የተለያዩ የህላፊነት ቦታዎች ቅድሚያ እንደሚሰጧቸው የተናገሩት ወታደራዊ ምንጮቻችን፣ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጎች ለሚታዩት ከሌላ ብሄረሰብ ለተውጣጡ የሰራዊት አባላት ግን እንኳንስ የተለያዩ ጥቅሞች ሊሰጣቸው ቀርቶ በወር ከሚያገኙት ደሞዝ ላይ በሰበብ አስባቡ እንደሚቆረጥባቸው ተናግረዋል።

እነኘህ አነደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ የሚታዩት የሰራዊቱ አባላት ቤተሰቦች በቀን አንድ ጊዜ እንኳ ተመግበው ለማደር በማይችሉበት ደረጃ ሲገኙ፣ የአንደኛ ደረጃ ዜጋ ቤተሰቦች ግን ከቪላ ቪላ፣ ከመኪና መኪና እያማረጡ እንደሚኖሩ ሰራዊቱ ጠንቅቆ ማወቁ አሁን ለተፈጠረው ችግር ዋንኛ መንስኤ መሆኑን ገልጸዋል።

የወያኔ የጦር አዛዦች በደርግ ዘመን ያገለገሉ የሰራዊት አባላትን ካባረሩ በሁዋላ፣ በመቀጠልም የሁለተኛ ደረጃ ዜጋ መኮንኖችን በተለይም የአማራና የኦሮሞ ተወላጅ መኮንኖችን ለማባረር እቅድ እንዳላቸው ምንጮቻችን ተናግረዋል። ወያኔ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የሚታየውን ሽኩቻ ያበረደ መስሎት፣ እነ ጄ/ል ተፈራ ማሞን ወደ ወህኒ ቢወረውርም፣ ከጄኔራሉ እስራት በሁዋላ በመከላከያ ውስጥ ያለው ሽኩቻ ተጠናክሮ መቀጠሉን ምንጮቻችን ተናግረዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ በቅርቡ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ካሉት 62 ወታደራዊ አዛዥነት የስልጣን እርከኖች 58ቱ በህወአት ነባርና አድስ ታጋይ የትግራይ ተወላጆች መያዛቸውን መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን፣ ዘገባው ከቀረበ በሁዋላ በመከላከያ ውስጥ ትልቅ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑንም ለማወቅ ተችሎአል።

## ባለፈው አመት ታህሳስ አሳፋሪ ሽንፈት ... ከገጽ 1 የዞረ

የወያኔ ወታደሮችን የጫኑ በርካታ ወታደራዊ መኪናዎች በአከባቢያቸው እንደተመለከቱ የአይን እማኞች ተናግረዋል።

ወያኔ የሶማሊያን ድንበር አቋርጥ የገባው በተደጋጋሚ ውጊያ ፋታ የነሱትን የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር ተፋላሚዎች ለማደን እንደሆነ የፓለቲካ ተንታኞች ለሬዲዮ ፍራንስ ኢንተርናሽናል ተናግረዋል።

የሶማሊያን ድንበር አቋርጦ የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር ተፋላሚዎችን ሊያድን የመጣው የወያኔ ጦር ለዘመቻው ከፍተኛ ወጪ ቢያወጣም ምንም እንዳላገኘ እና ኪሳራን እንደተከናነበ ታውቋል።

ኢትዮድያዊያንን በዘረኛ አገዛዙ እና መረን በለቀቀው ጭካኔው እያሰቃየ ያለው የፋሺስቱ የወያኔ ብድን የሀገር ውስጥ ሳያንሰው የጎረቤት ሀገራትን ዜጎችን መናከሱን በስፋት ተያይዞታል።ከኦጋዴን ነጻ አውጪዎች ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን ንጹሀን የሶማሊያ ሲቪሎችን ድንበራቸውን አቋርጦ፤መንደራቸው ድረስ እየሄደ የኦጋዴን ነጻ አውጪዎችን ውለዱ እያለ ንጹሀንን የሚያሰቃየው ወያኔ የያዘው የጥፋት መንገድ በርካታ ጠላቶችን እያተረፈለት እንደሆነ ተገልጿል።

ወያኔ ባለፈው ሳምንት ረብእ መስከረም 27 በራስ ገዝ አስተዳደር ያለችው ፑንትላንድ ውስጥ የሚገኝ አንድ መንደር ውስጥ ያለን ቤት ጨለማን ተገን አድርጎ ሰብሮ ገብቶ የቤቱን ባለቤት በጥይት ማቆሰሉ እና ከቤቱ ባለቤት ጋር የነበረውን ሰውም በጥይት አቁስሎ ባልታወቀ ስፍራ ጥሎት መሸሹን ቢቢስን ጠቅስን መዘገባችን አይዘነጋም።

በኦጋዴን ክልል ንጽሀን የሀገራችንን ሰዎች አዛውንት እና ህጻናትን ሳይል የኦጋዴን ግንባር ተዋጊዎችን ሸሽጋችሓል እያለ በግፍ የረሸነው፤በጅምላ መንደር ያቃጠለው እና ሴቶች የደፈረው የወያኔ ጦር በአለም አቀፍ የሰብአዊ እና የዘረ ፍጅት ተከላካይ ተቋማት በጦር ወንጀል እና የሰው ዘር ማጥፋት መከሰሱ የሚታወስ ነው።

## አምባሳደር ተብየው ሳሙኤል አሰፋ ... ከገጽ 1 የዞረ

እነዚህ ሁለት ግለሰቦች ከወያኔ ባለስልጣናነት ጋር ሲነጻጸሩ በተሻለ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ቢሆንም፣ ባላቸው የሆድ አምላኪነት ባህሪ የተነሳ የምሁርነታቸውን ካባ አውልቀው በመጣል ለጫካ ገገሮች ራሳቸውን ያሳደሩ መሆናቸው ይታወቃል። ኢትዮጵያውያን "ሆዱን የወደደ ማእረጉን ይጥላል" የሚሉት አባባል ለእንድርያስ እሸቴና ለሳሙኤል አሰፋ ትክክለኛ መገለጫ መሆኑን ብዙዎች የሚናገሩ ሲሆን፤ እንድርያስ ና ሳሙኤል ከሆድ አምላኪነታቸው በተጨማሪ ራሳቸውን ዘወትር መለኪያ ውስጥ ዘፍዝፈው ካላደሩ ለአንድም ቀን በህይወት ለመቆየት የማይችሉ አሳዎች በመሆናቸውም ይታወቃሉ።

## ቴዲ የተከለከለውን ዘፈን ታዳሚው ዘፈነለት ... ከገጽ 1 የዞረ

የኢትዮጵያን ወጣቶች በገንዘብ፣ በስራና በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች በመደለል ደጋፊዎቹ ለማድረግ ላለፉት 5 አመታት ደፋ ቀና ሲል የነበረው የወያኔ አገዛዝ፣ በዚህ የዕሁዱ የወጣቶች ድርጊት በእጅጉ መደናገጡንም ለማወቅ ተችሎአል። አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ በየጊዜው በቴሌቪዥን እየቀረበ ወጣቶችን ለመማረክ ያደረገው ጥረት እንደተሳካ በተለያዩ የወያኔ ስብሰባዎች ላይ ሲገለጽና አሰራሩም ሲወደስ ቢቆይም፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ግን የመለስን የአምስት አመት ልፋት ከንቱ በሚያስቀር ሁኔታ በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ሲገልጹ አምሽተዋል። የመለስ አገዛዝ ለቴዲ አፍሮ ኮንሰርት እንዲያዘጋጅ የፈቀደው ከሁለት ሳምንት በፊት የተከበረውን የደመራ በአል ያለተቃውሞ መጠናቀቁን ከተመለከተ በሁዋላ መሆኑን ምንጮችን ዋቢ አድረጎ የተናገረው ዘጋቢያችን፣ በዚያን ጊዜ ወጣቶቹ የቴዲ አፍሮ ዝግጅት እንዳይቋረጥ በመፍራትና ተቃውሞዋቸውንም በቴዲ ዝግጅት ላይ ለማሰማት በመወሰን በይደር አቆይተውት እንደነበር ዘግቦአል። በህዝቡ ዝምታ በመጽናናት የአዲስ አበባን ህዝብ አሳምኜዋለሁ እያለ ሲዝት የነበረው ወያኔ በዚህ ያልተጠበቀ ድርጊት በመደናገጡ አባሎቹንና የጸጥታ ሀላፊዎቹን ላስቸኳይ ስብሰባ መጥራቱም ታውቋል።

ወያኔ ኢትዮጵያውያንን በግዴታ የአባልነት ፎርም በማስሞላት የዘንድሮውን የይስሙላ ምርጫ ከ 90 በመቶ በላይ በሆነ ድምጽ ለማሸነፍ አቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ የቴዲ አፍሮ ኮንሰርት ግን፣ ህዝቡ አሁንም ከወያኔ ጋር ሆድና ጀርባ መሆኑን አሳይቷል ብሎአል ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ ታዋቂ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች።

በቴዲ አፍሮ የሙዚቃ ዝግጅት ላይ የተገኙት ታዳሚዎች ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች መምጣታቸው የተናገረው ሪፖርተራችን፣ ቴዲ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ዘፈኖች እንዳይዘፍን በመከልከሉ ታዳሚዎች ብስጭታቸውን ሲገልጹ እንደነበርና "ጃ ያስተሰርያል"ና ሌሎችንም ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ሙዚቃዎች በራሳቸው ድምጽ ያንጎራጎሩት ወሳኔውን መቃወማቸውን ለመግለጽ እንደነበርም ተናገሯል። ይህ የስተዲየሙ ኮንሰርት በቴለቪዠን ለህዝብ እንዳይተላለፍ የተከለከለው እድምተኛው ስሜቱን በእንዲህ አይነት ሁኔታ የሚገልጽ ከሆነ ከስፍራው ውጪ ያለው ህብረተሰብ እንዳያውቅ ተፈልጎ እንደሆነ ለወያኔ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ።

በተያያዘ ዜና በሙዚቃ ዝግጅቱ ላይ ከተሳተፉት መካከል በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታስረው መፈታታቸውን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመለከተ። ወጣቶቹ በአዲስ አበባ የትራንስፖርትና መንገዶች ባለስልጣን ቅጥር ግቢ ውስጥ ታስረው በቆዩበት ጊዜ ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው የደረሰን መረጃ ያመለከተ ሲሆን፣ የሙዚቃ ዝግጅቱ ከምሽቱ አምስት ሰአት ካለቀ በሁዋላ እስረኞቹ ወደ አዲስ አበባ ፖሊስ 6ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተዛውረው ሌሊቱን በዚያ እንዲያሳልፉ ተደርገዋል። በማግስቱ ከጠዋቱ 3፡ ተኩል አካባቢ ደግሞ ሁሉንም እስረኞች በዲጂታል ካሜራ ፎቶ ግራፍ እያነሱና የእጅ አሻራቸውን እየወሰዱ ለቀዋቸዋል።

ታስረው ከተለቀቁት መካከል አቶ ወንዴ የተባሉት የአዲስ አበባ ነዋሪ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፣ የፌደራል ፖሊሶች ከቀኑ በ9 ሰአት ወደ አዲስ አበባ ትራንስፖርታና መንገዶች ባለስልጣን ግቢ ወስደው ድብደባ ፈጽመውባቸዋል። ለመታሰራቸው ምክንያት የሆነው የኢትዮጵያን ካርታ፣ ሰንደቅ አላማና የቴዲ አፍሮን ምስል የያዘውን ቲሸርት በመልበሳቸው መሆኑን የተናገሩት አቶ ወንዴ፣ አንዳንዶች የወያኔ አርማ ያረፈበትን አዲሱን ባንዲራ እንኳ ለብሰው ሲመጡ "እንዴት ለአንድ አዝማሪ ባንዲራ ትለብሳላችሁ" ተብለው እንደተገረፉ አስረድተዋል። አብዛኞቹ እስረኞች ከፍተኛ ድብደባ ስለተፈጸመባቸው በማግስቱ ለመራመድ እንኳ ሲቸገሩ መታየታቸውን የተናገሩት አቶ ወንዴ፣ የወያኔ ባለስልጣኖች ለቴዲ አፍሮ ያላቸውን ጥላቻ በግልጽ ሲናገሩ መስማታቸውን መስከረዋል።ሁለት ነጋዴዎችም አብረዋቸው ታስረው እንደነበር የገለጹት አቶ ወንዴ፣ ለሽያጭ ያቀረቡዋቸው አንድ አይሱዙ መኪና ቲሸርቶች በወያኔ ባለስልጣናት እንደተወሰዱባቸውና በሰዎቹም ላይ ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑን አክለው ገልጸዋል።

በቅርቡ የወያኔ ገገሮች የህዝቡን ድጋፍ ያገኘን መስሎዋቸው ከልባቸው የማያምኑበትን ባንዲራ ቀን አሁን ቀን ለማክበር ስተዋቸው የማያምኑበትን ባንዲራ ቀን በአል ቀን ሰጥተው ማክበራቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ባንዲራውን ከእነሱ ደጋፊዎች ውጭ ያሉት ዜጎች ሲይዙት ግን ደማቸው እንደሚፈላ ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለማረጋገጥ መቻሉን የአይን እማኞች ተናግረዋል። አንድ አስተያየት ሰጪ " ትናንት የባንዲራ ቀን ተከበረ ተብሎ ተነገረ፤ ዛሬ ደግሞ ባንዲራ የያዘ ሁሉ እንደ ጠላት ታይቶ እስር ቤት ተወረወረ። እንግዲህ እንዲህ አይነቱን መደናበር ምን ይሉታል?" ሲሉ አግራሞታቸውን ገልጸዋል።

የመለስ አገዛዝ ላለፉት በርካታ አመታት በየአመቱ ከአስር በመቶ በላይ ዕድገት አስመዝግቢያለሁ እያለ ቢደነፋም በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከሁለት መቶ ሺ በላይ የጎዳና ተዳዳሪዎች እንደሚኖሩና በዚህ ስሌት መሰረት ከ ፲፡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ማካከል አንዱ የጎዳና ተዳዳሪ ሆኖ አያለ ፣ በቅርቡ በአገሪቱ የሚታየውን ረሀብና ችጋር በመሸሸ ወደ አዲስ አባባ የሚፈልሱት ዜጎች ቁጥር ተጨምሮበት የህዝቡ የኑሮ ደረጃ በምን ያህል ፍጥነት እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ እንደሚገኝ አገዛዙ ለመረዳት ምንም ፍላጎት የለውም ተብሎአል። ግንቦት 7 በአገራችን የሚታየውን ድህነት መቅረፍ የሚቻለው፣ በተደናበረ የኢኮኖሚ ፖሊሲው አገሪቱን ወደ መቀመቅ እየከተታት ያለውን ዘረኛውን የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ ሲቻል ብቻ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጽ መቆየቱ ይታወሳል።


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢያቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ያይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661